የሰ/መ/ቁ. 162771

ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** አቶ ብርሃኑ ገለታ

**ተጠሪዎች-** 1. ወ/ሮ ደስቱ ደምሴ

2. አቶ ሀብታሙ ደምሴ

3. አቶ ቦርጃ ገለታ

4. አቶ ጥላሁን ገለታ

5. አቶ አዱኛ ገለታ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን፣ የተጀመረዉም በምሥ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች በአሁን ከ1-3ኛ ተጠሪዎች ላይ ባቀረበዉ የአፈፃፀም ክስ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ችሎት በመ/ቁጥር 209742 ላይ በቀን 04/05/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጸምለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ በመግባት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ እና ለአፈፃፀም መነሻ የሆነዉ ዉሳኔ በእነርሱ የመቃወም አቤቱታ መነሻ በማድረግ በተደረገ ክርክር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34459 ላይ በቀን 02/02/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ የተሻረ መሆኑን ጠቅሰዉ የሚፈጸም ዉሳኔ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ለአፈፃፀም መነሻ ያደረጉት ዉሳኔ የአሁን 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓ ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረቡትን መቃወሚያ ተከትሎ በተደረገ ክርክር በከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34459 ላይ በቀን 02/10/2009 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የተሻረ መሆኑን ጠቅሶ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ዉሳኔ

በማጽናቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ነሐሴ 18 ቀን 2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታ 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በሌላ መዝገብ ላይ የክርክር ተከፋይ ሆነዉ ገብተዉ በኋላ በእራሳቸዉ ጊዜ ክርክሩን አንፈልግም ብለዉ ከወጡ በኋላ ዉሳኔ ተሰጥቶ አፈፃፀም ከተከፈተ በኋላ ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ በመቀበል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 209742 ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ታርሞ እንዲወሰንላቸዉ አመልክተዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከላይ በአጭሩ የተገለጸዉ የጉዳዩ አመጣጥ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የአመልካችን የአፈፃፀም ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉን ዉሳኔ አግባብነት ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰዉ አመልካች ላቀረቡት የአፈፃፀም ክስ መሠረት ያደረጉት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት በመ/ቁጥር 209742 ላይ በቀን 04/05/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት አፈፃፀም የተጠየቀበት ንብረት የአመልካች ነዉ ተብሎ የተሰጠን ዉሳኔ ሲሆን፣ ይህም ዉሳኔ የምሥ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34459 በቀን 02/02/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የተሰጠ ዉሳኔ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይሁንና ለአፈፃፀም ክርክሩ መነሻ የሆነዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተሰጥቶ አመልካች የአፈፃፀም መዝገብ ከከፈተ በኋላ፣ የአሁን 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ለዋናዉ ክርክር መነሻ ከሆኑት ንብረቶች ላይ የዉርስ ድርሻ ያላቸዉ መሆኑን በመጥቀስ አስቀድሞ ተሰጥቶ የነበረዉ ዉሳኔ ተነስቶ በክርክሩ ጣልቃ ገብተዉ እንዲከራከሩ እንዲፈቀድላቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ በመቀበል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ግራ ቀኝን አከራክሮ በ02/10/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በመ/ቁጥር 34459 ላይ በቀን 02/02/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ በመሻር ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነዉ ንብረት ወራሾች የሆኑት የአመልካች፣ የ4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የጋራ ሀብት ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ዉሳኔ ሥርዓቱን ጠብቆ በሌላ በይግባኝ የተሻረ ስለመሆኑ በአመልካች የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ችሎት በሰጡት መልስ ንብረቱን የጋራቸዉ በማድረግ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በ02/10/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝ ተቀባይነት ማጣቱን ጠቅሰዉ የተከራከሩ ሲሆን፣ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ ይህን ክደዉ አልተከራከሩም፡፡ ይህ በአጠቃላይ የሚያሳየዉ አመልካች ለአፈፃፀም መሠረት ያደረገዉ ዉሳኔ በሌላ ዉሳኔ የተሻረ መሆኑን ነዉ፡፡

ፍርድ እንዲፈጸምለት ጥያቄ የሚቀርብ ወገን ሊፈጸም የሚችል ፍርድ ስለመኖሩ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት መሆኑ እና ፍርድን የሚያስፈጽም ፍርድ ቤትም ሊፈጸም የሚችል ፍርድ ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 378 እና ተከታዮች ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ የፍርድ አፈፃፀም ስለ ፍርድ አፈፃፀም የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የማስፈጸሚያ ስርዓቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓትን ህጉን መሠረታዊ ዓላማ ተከትሎ እንዲፈጸም በሚያስችል አኳያ ትርጉም ሊሰጠዉ የሚገባ ነዉ፡፡ የፍርድ አፈፃጸም መደበኛ ክርክር ከሚመራበት ስርዓት የተለየ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ የእራሱ የሆነ ሥ/ሥርዓት የተቀረጸለት በመሆኑ፣ እንዲሁም በዋናዉ የክርክር ሂደት የተፈጸመን ግድፈት

በአፈፃፀም ክርክር ሂደት መለወጥ ወይም ማሻሻል ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ እስካልተለወጡ ወይም እስካልተሻሻሉ ድረስ የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተፈፃሚ ሆነዉ ሊቀጥሉ ይገባል የሚለዉን የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉን መርህ (በተለይ የህጉ አንቀጽ 212 ይመለከቷል) የሚያፋልስ ዉጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለሆነም በዋናዉ ክርክር ሂደት የተፈጸሙ የክርክር ሥነ ሥርዓቶች ወይም ዉሳኔዎች ምንም እንኳ ግድፈት ቢኖርባቸዉም በአፈፃፀም የክርክር ሂደት የሚታረሙ አይደሉም፡፡ ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረዉ ዉሳኔ በድጋሚ ታይቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት መሻሩ፣ እንዲሁም አመልካች እንደሚሉት 4ኛ ተጠሪ በዋናዉ ክርክር ላይ ተከራካሪ ሆኖ ገብተዉ በእራሳቸዉ ጊዜ ክርክሩን አልፈልግም ብለዉ ከተዉ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቀበሉ ስህተት ነዉ ቢባል እንኳ ይህ ስህተት መታረም ይችል የነበረዉ በመደበኛዉ የክርክር ሂደት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ በተዘረጋዉ የክርክር ሂደት እንጂ በአፈፃፀም የክርክር ሂደት ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ላቀረቡት የአፈፃፀም ክስ መሠረት የሆነዉ እና በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 209742 ላይ በቀን 04/05/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34459 በቀን 02/10/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሻረ መሆኑን አረጋግጦ ለአመልካች ሊፈጸም የሚችል ዉሳኔ የለም በሚል በምሥ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ በአብላጫ ድምጽ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉ ሳ ኔ</u>**

1. የምሥ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46706 በቀን 08/05/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 214184 በቀን 16/08/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 284911 በቀን 26/10/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት በአብላጫ ድምፅ ፀንተዋል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት**

## የልዩነት ሃሳብ

ስሜ በተራ ቁጥር ሦስት ላይ የተሠየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሀሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍራለሁ፡፡

ክርክሩ በአፈጻጸም ደረጃ ያለ ሲሆን ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳሁት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ተቃውሞ ያቀረቡበትን ፍርድ አመልካች አስቀድመው ይግባኝ በማቅረብ ውሳኔው እንዲሻር አድርገዋል፡፡ ይህም ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ተቃውሞ ያቀረቡት ለተቃውሞ መነሻ የሆነው ፍርድ በይግባኝ ከተሻረ በኋላ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች የፍርድ ባለመብት ሆነናል የሚሉት ለተቃውሞ መሠረት የሆነው ፍርድ ከተሻረ በኋላ ወደ ክርክር በመግባት የተሠጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ውሳኔው በይግባኝም ታይቶ የጸና መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶችም ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ባለመብት የሆኑበት ፍርድ የጸና ስለሆነ ሊፈጸም ይገባል በማለታቸው የቀረበ የሠበር አቤቱታ ነው፡፡

አከራካሪው ጭብጥ ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በፍርድ ባለመብት የሆኑበት ሊፈጸም የሚችል የጸና ፍርድ መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ የአፈጻጸም ችሎት ጉዳዩን መምራት ያለበት የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችና ለአፈጻጸም መሠረት የሆነውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሲሆን ውጤቱም ሠዎች በፍርድ ያገኙትን መብት ማስፈጸም ነው፡፡

የአፈጻጸም ችሎት በመርህ ደረጃ የቀረበን ውሳኔ የማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ በህግ ዳኝነት ለመሥጠት ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ፣ የዳኝነት አካሉ በሕግ አግባብ የተቋቋመ፣ ሊያስችሉ የተሠየሙ የዳኞች ቁጥር የተሟላ መሆኑ እና የውሳኔው መሠረት የሆነው ነገር ሕልውና ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥና በአጠቃላይ ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ የጸና መሆኑን መመርመር አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ተቃውሞ ያቀረቡበት ፍርድ አስቀድሞ የተሻረ እና ሕልውና የሌለው መሆኑ አላከራከረም፡፡ በተሻረ ፍርድ መሠረት አድርጎ የሚሠጥ የወጭና ኪሣራ ውሳኔ፤ ውሳኔው

ራሱን ችሎ በይግባኝ መሻር ሳያስፈልገው ለውሳኔው መሠረት የሆነው ፍርድ ሲሻር አብሮ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ በተመሳሳይ ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ተቃውሞ ያቀረቡበት ፍርድ በይግባኝ የተሻረ እና መብትን ሊነካ የማይችል ሕልውና የሌለው ፍርድ ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የቀረበ የመቃወም ማመልከቻ ውጤቱ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) የተመለከተ ሲሆን ይህም ፍርዱን ማጽደቅ፣ መለወጥ፣ ማሻሻል ወይም መሠረዝ ነው፡፡ የተሻረ ፍርድ መብትን ሊነካ አይችልም፡፡ የሚጸድቅ ወይም የሚለወጥ ፍርድ አስቀድሞ ተፈጻሚነት ያለው እና የፀና ፍርድ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ያልጸና ፍርድ ሊለወጥ ወይም ሊጸና ስለማይችል ነው፡፡ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ይህን ተረድቶ ተቃውሞውን ወድቅ ማድረግ ይጠበቅበት ነበር፡፡ ይህ ሳይሆን ሕልውና በሌለው ፍርድ ላይ ተመስርቶ መብታቸውን ይነካል ወይስ አይነካም በማለት አከራክሮ መወሰኑ የተቃውሞው መሠረት የሆነው የቀድሞ ፍርድ የተሻረ እና ተፈጻሚነት የሌለው በመሆኑ የተሻረውን ፍርድ ተከትሎ የተሠጠው ፍርድ በተመሳሳይ ውጤት የሌለው የማይጸና ውሳኔ ያደርገዋል፡፡

አመልካች ፍርዱ ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች የተቃወም መሠረት ከመሆኑ በፊት ፍርዱን በይግባኝ በማሻር ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ባለመብት ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ፍርዱ ከተሻረ በኋላ ክርክር ተደርጎ የተሠጠው ውሳኔ ባለመብት የሚያደርጋቸውና እንደጸና ፍርድ ከተቆጠረ ሁለት እርስ በእርሱ ተቃርኖ ያለው የፀና ፍርድ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በአንድ የክስ ዳኝነት መሠረት ላይ ሁለት የጸና ፍርድ ሊኖር አይችልም፡፡ ሁለት የፀና ፍርድ ሊኖር የሚችለው ዋናው ፍርድ ከተሠጠ በኋላ ጉዳዩ በአዲስ የክስ ዳኝነት ቀርቦ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ነው የሚል መቃወሚያ ባለመቅረቡ ወይም ፍርድ ቤቱ በፍርድ አስቀድሞ ማለቁን ባለማወቁ አዲስ ፍርድ በተመሳሳይ ጉዳይ ከተሠጠ ነው፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ ያለው አንድን ክስ መሠረት ያደረገ አንድ የጸና ፍርድ ብቻ ነው፡፡ ሁለተኛው ውሳኔ በተሻረ ፍርድ ላይ የተሠጠ ስለሆነ ብቻውን የሚቆም አስገዳጅ ፍርድ አይደለም፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት የጸና ፍርድ አለ ከተባለ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ እና በሕግ አግባብ ባለመብት የሆኑትን የአመልካች መብት የሚጎዳ ነው፡፡ አመልካች በፍርድ ያረጋገጡትን መብት ሳይፈጸምላቸው ፍርዱ ያለውጤት ቀሪ ሊሆን ስለማይገባ የሥር ፍርድ ቤቶች ከ3ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች የመቃወም ማመልከቻ ካቀረቡ በኋላ የተሠጠው ውሳኔም የጸና እና ሊፈጸም የሚችል ነው ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ መሠረታዊ

**የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ውሳኔው ሊታረምና አመልካች ብቸኛ የፍርድ ባለመብት ሆነው ፍርዱ ሊፈጸም ይገባል በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡**

**የማይነበብ  የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት ፡፡**

***ቅ/ወ***